# ልፋለመው እንጂ ትግሥቱ ሰለቸኝ

ሀገሬን ለማዳን ቀኑ ቢርቀኝም

ፈተናው በርክቶ ጭንቀት ቢከበኝም

አንገቴን ደፍቼ ማልቀሴ አልቀናኝም

ለቅሶዬ የፍቅር ቢሆን... አይገርመኝም

የልቤ ቋጠሮ...አልተፈታልኝም?

ውስጤ ቅጥል ብሎ ደህና ቢመስለኝም

ልቤ ግን ተጽናንቶ ቀና-በል ቢለኝም

ቀን ይቆጥር ይዞአል... ግን አልነገረኝም?

የልቤን ማን አውቆ፣ ኃቁን ይንገረኝ

ፍቅር አስጨንቆኝ ፣ፍራኃት ተናንቆኝ

ቀን ይፍታው ማለቴ፣ ፍርኃት መስሎብኝ

ትግስት እንደ ፍርኃት፣ ለምንስ ታየብኝ?

ወኔዬ ገንፍሎ እንዲህ እየናጠኝ

በደሉ በዝቶብኝ ግፉም አንገሸግሾኝ

በገዛ አገሬ ተሰድቦ፣ተንቆ፣ሕይወት ሰቀጠጠኝ

ተዋርዶ ከመኖር ሞቴን አስመረጠኝ

ልፋለመው እንጂ ትግሥቱ ሰለቸኝ

እረጋ በል ቢሉኝ መቼ ሊገባኝ

ነፃነት አጥቸ መብት ሳይኖረኝ

ልቤም ተቸግራ ወጥሮ ይዞኝ

እምቢ ልበልና ወንድነት ይውጣኝ

ይፈንቅል ይታገል ይተርተርልኝ

የበጠው ይፈንዳ ቀኑ ናፈቀኝ

፩፩/፱፺/፩፩